# <u>ቃሉን ለእኔ ሰጠኝ</u>

ወይራው አበበ 2003

እንደ ወንድሞቻችን እንደ እህቶቻችን፣
እሱም ሰጠኝ የእምነት-ፍቅር ቃሉን፡፡
እኔ ምንተዳየ ተድላ በረከቱን ልሸከም ብነሳ፣
ስጦታው ትልቅ ነው በጣም ግዝፍ የነሳ፣
እዩ ተመልቱ እዲህ ያለ ልገሳ፣
እኔ አልገባኝ ሞኙ አልተረዳሁት፣
የተድላን ስጦታ ቃል በቃል አየሁት፡፡

ቃሉ እንዳይረሳኝ እንዳይዘነጋኝ፣
በፍቅር ወለላ ጀምሮ አስጨረሰኝ፡፡
ለማወቅ ፈልጌ የቃል ስጦታ ምስጢርን፣
የትርጓሜው ስፋት ጥልቀትን፣
የእሱ የሳሙኤልን ቃል ሳስተውለው፣
ቃሉ ሥጋን ተዋዳው፡፡

ለወገን አርነት ለሀገር ነፃነት መሞት፣
ሞት አይባልም ዳግም ትንሳኤ ልደት፡፡
ሳሙኤል ልክ ለእናቱ እንዳለው ፍቅር፣
እዚህም እዛም እህት አፈራ በእምነት ጠንካራ ድር፡፡
የወንድሞቹም ብዛት አይዘለቅም በቁጥር፡፡

አገሩ ኢትዮጵያን በጣም ይወዳል፣
ጠላት ፍልፈል ተባይዋን እጅግ ይጠላል፣
ግሮ እሚኖርን በላቡ አደርን አብልጦ ይወዳል፣
በዝባዥ ቱሀን መዥገሯን አፍርጦ ይደፋል፡፡
ሀብት ንብረቱ ጎጆ ትዳሩ፣
ህዝቢና ኢትዮጵያ እናት አገሩ፡፡

ካወረሰኝ ከቃሉ ሥጋና ደም አገኘሁኝ ሦስት፣
ከሁሉም በላይ በቃል ኪዳን ከዛ እስከዚያ መቆም በጽናት፣
ደግሞም መውጣት ደግሞም መውረድ ደግሞም መንዝ በትግስት፣
ባንዳ ሹምባሹን ሆዳም ፈሪውን ዋሾ ፌሽካውን፣
ቀፎ ምሁሩን ፋሽስት ገራፊን ሰቃይ ገዳይን፣
አንቅሮ መትፋት አንጓሎ መጣል ውሸትን ጥሎ፣
ሀቅ ምርኩዙን ሀቅ ስንቁን እውነትን አዝሎ‹
የትግሉ ነው ህይወቴን ዘምሮኝ ዘምር ብሎኝ፣
አገጩን ይዞ እራሴን አሸቶ ስሞኝ፣
ቃሉን በአደራ በቃሉ ሰጠኝ፡፡

( ለሳሙኤል ዓማየሁ መታሰቢያ)